ዴሞክራሲያ

የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ልሳን

**ዴሞክራሲያ ቅጽ. 38 ቁጥር 6** **ሐምሌ 2005 ዓ.ም**

# <u>አላቋርጥ ያለው አምባገነንት፣ አልከስት ያለው ዴሞክራሲ በኢትዮጵያ</u>

ኢትዮጵያ በጥንታዊ ስልጣኔዋ፣ የረጅም ጊዜ ታሪክ ቅርስ ባለቤት፣ ህዝቧ የበርካታ ባህል ፣ ወግና ልምድ ተቋዳሽ ፣ የነጭ ወራሪ ኃይልን ደግማ ደጋግማ ድባቅ የመታች፣ የጥቁር ህዝብ መመኪያ፣ ተስፋና አለኝታ፣ የሰው ልጅ ቅሪት የተገኘባት የድንቅነሽ አገር፣ እንደሆነች በየጊዜው የተገለጸ መሆኑ የታወቀ ነው። ይህ ግን የኢትዮጵያ አንዱ ገጽታ ነው። አትዮጵያውያንን ሁሉ የሚያኮራ ገጽታ። ይሁን እንጂ በሌላው ገጽታዋ፣ ባላሰለሰ ብልሹ አስተዳደር የተነሳ፣ የኢኮኖሚ እድገት ኋላ ቀርነት በጉልህ የሚታይባት፤ በትምህርት፣ በሳይንስና በሥነ ጥበብ …ወዘተ ወደ ኋላ የቀረችበት ፤ አብዛኛው ህዝቧ በድህነት ማቅ ኑሮውን የሚገፋበት፤ ረሃብ፣ እርዛት ከመጠን በላይ የነገሱበት፤ ሰው እንደ ሰው ሆኖ፣ እንዳሻው፣ በነጻነት የሚቧርቅባት አገር እንዳልነበረችና እንዳልሆነች የሚካድ አይደለም። ይህ አስከፊ ገጽታዋ፣ በውስጡ ለዘመናት ተሸክሟቸው የቆዩት በርካታ ጉዳዮች፣ ማለትም የአስተዳደር ብሉሽነት፣ የፍርድ እጦትና አድሏዊነት፣ የሃይማኖቶች እኩልነት መጥፋት፣ በልዩ ልዩ ብሔረሰቦች መካከል ሊኖር የሚገባው እኩልነት መጓደል፣ በፖለቲካዊ፣ኤኮኖሚያዊና ማህበራዊ ዘርፍ ተንሰራፍቶ ለበርካታ ዓመታት የቀጠለው ኢፍትሃዊ ድርጊት፣ ምንም እንኳን በልዩ ልዩ ግፍ በተሞላባቸው መንገዶች በመጠቀም ቀጣይነት ኖሮት እንዲጓዝ ገዢው ክፍል ያላሰለሰ ጥረት ቢያደርግም፣ ለዘመናት የዚህ አስከፊ ድርጊት ሰለባ ሆኖ የቆየው የኢትዮጵያ ሰፊ ህዝብ ከእንግዲህስ መገዛቴ ያብቃ ሲልና የግፉም አገዛዝ እንደወትሮው የመግዛት አቅሙ ሲሟጠጥ፣ እነሆ አገሪቱን ከዳር እስከዳር ያናወጠ የለውጥና የብሩህ ተስፋ እንቅስቃሴ እንደ ኢትዮጵያ ዘመን አቆጣጠር በካቲት 1966 ዓመተ ምህረት እንዲከሰት ምክንያት ሆነ። የሚታወቀውን መድገም ቢሆንም፣ ይህ ሁኔታ በዚያ ምድር እንዲሰፍን መንገዱ ሁሉ አልጋ በአልጋ፣ ቄጤማ የተጎዘጎዘበት፣ በሆታና በእልልታ የታጀበ፣ ጮቤ የተረገጠበት አልነበረም። የእነመንግሥቱና የግርማሜ ንዋይን፣ የበርካታ የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎችን፣ ቁጥራቸው በውል ያልታወቀ አርሶ አደሮችንና፣ ላብ አደሮችን ባጠቃላይ ስማቸውን እዚህ ላይ ለመጥቀስ የማይቻለውን የጭቁኖችና የተበዝባዦችን ህይወት በሂደቱ አስከፍሎ የተወለደ ብሥራት ነበር።

ያ ብሥራት ከእንግዲህ ለዝንት ዓለም በተከታታይ ሳያቋርጥ እንዳሻው ሲፈልጥ ሲቆርጥ የቆየውን የዘውድ አገዛዝ ዳግም እንዳይመለስ አድርጎ አንኮታኮተው። በምትኩ፣ ያሻኝን የምሆንባት፣ ነጻ ሃሳባችንን የምገልጽባት፣ በነጻ የምንደራጅባት፣ የምንፈልገውን የምንመርጥባት፤ የማንፈልገውን የምናወርድባት ፣

በምድሪቱ ሁሉ እንደልባችን በነጻነት የምንቀሳቀስባት፣ የመጻፍ የመናገር መብታችን የተረጋገጠባት፣ እንዲያም ሲል የሥልጣን ምንጭነታችንና ባለቤትነታችን በተግባር ዕውን የሆነባት ሕዝባዊ ዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያን እመሠርታለን ብሎ ሕዝባችን መነሳቱንና ስንቁንም መሰነቁን፣ ለዓለም ሁሉ አስታወቀ። ከመቅጽበት፣ ተሸብበው የነበሩ አንደበቶች፣ ያሻቸውን ሊጽፉ፣ ሊናገሩ የሚፈልጉ ተለጉመው የቆዩ ሚሊዮን አዕምሮዎች፣ ...ወዘተ ምድሪቱን ያጥለቀለቀው የነፃነት አየር ፣ ተቋዳሽ የመሆን ዕድል ገጠማቸው። በሃገሪቱ ለመጀመሪያ ጊዜ ከዩኒቨርስቲ ቅጥር ግቢ ውጪ ልዩ ልዩ የሃሳብ ፍጭቶች፣ አስተያየቶች፣ ውይይቶች፣ መጣጥፎች እንደአሸን ፈሉ። በአጭር ጊዜ ውስጥ፣ በስነጽሁፍ፣ በኪነጥበብ፣ በፖለቲካ ንቃት፣ ከፍ ያለ እምርታን ያስመዘገቡ፤ በርካታውን የዚያን ዘመኑን ትውልድ ያሳተፉ እንቅስቃሴዎች ገዝፈው ታዩ። ኢትዮጵያውያን ይህን ታሪካዊ ዘመን፣ እንደ ድንገት ደራሽ፣ የመልካም ጊዜ ጅማሮ፣ የብሩህ ተስፋ አመልካች፣ ...ወዘተ አድርገው ወሰዱት። የነፃነትን አየር እየተነፈሱ የመጭውን ደግ ዘመን አማትረው ልባቸውን በደስታ ሞሉ፣ ፈነጠዙ፣ ጮቤም ረገጡ። ይህ በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠረውን ሥር ነቀል ለውጥ ፈላጊ ህዝብ ልብ በደስታ የሞላው፣ ብሩህ ተስፋንና ደግ ዘመንን የሰነቀው ሂደት ብዙም ሳይቆይ ወደ ፊት እንዳይገሰግስ ተገታ። አብዮቱም ተቀለበሰ። እነሆ ሰፊው ህዝብ ያኔ ያነሳውና ያስተጋባው ህዝባዊና ዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያን የመመስረት ዕቅድ ዛሬም ከአርባ አመት በኋላም ዕውን ሊሆን አልቻለም። አሁንም ጥያቄው ለምን?

ለዚህ ጥያቄ በሂደቱ ውስጥ የታቀፉት ተዋኒያን የሚኖራቸው መልስ አንድና አንድ ወጥ እንደማይሆን የሚጠበቅና ያለ ጉዳይ ነው። እዚህ ላይ የለውጡን እንቅስቃሴ ግቡ እንዳይደርስ የተረባረቡት ሁሉም ዓይነት አድህሮት ኃይላት የሚኖራቸውን መልስ የምናነሳው አይሆንም። የምናውቀውና የሰለቸም ስለሆነ፣ በምንም ዓይነት እሱ ጭንቀታችን አይደለም።

ወታደራዊው ፋሽስት፣ ኢትዮጵያን የሚጠሉና ለጥቅማቸው ብቻ የሚያስቡ የምሥራቁም የምዕራቡም ካምፕ፣ ያኔ በጫካ የነበሩት ወያኔና፣ የኤርትራ ግንባሮች፣ አንዳንድ ጎረቤት አገሮችና ለኢትዮጵያ የማይተኙት የአረብ አገሮች ጭምር ለዚህ ሂደት ቅልበሳ የነበራቸው ሚና ደግሞ ደጋግሞ የተነገረና የታወቀ ስለሆነ፣ በዚህም ላይ ብዙ ማለቱ አስፈላጊ አይሆንም።

ጥያቄውን ያነሳውና ለተገቢው መልስም ታግሎ፣ በርካታ መስዋዕትነት የከፈለው፣ ሰፊው ጭቁን ህዝብ (ላብ አደሩ፣ አርሶ አደሩ፣ ተራማጅ ምሁሩ፣ ተራማጅ መኮንኑ፣ ጭቁን ወታደሩ፣ ድርብ ተጨቋኟ ዜጋ፣ ወጣቱ፣ ...ወዘተ ሁሉ) ነው። ዜጎች፣ የለውጥ ሐዋርያዎች፣ የለውጡ ግንባር ቀደሞች አሁን ቆም ብለው የስር ነቀል ለውጥ እንቅስቃሴያቸው እስካሁን ግብ ላለመድረሱ በራሳቸውም ውስጥ እንዲያ እንዲሆን ያበቁ ጉድለቶች እንዳሉ ነቅሰው አውጥተው ሊገመግሙና ከዚያም ተገቢውን ትምህርት ቀስመው እርምትም አድርገው ለእንግዲሁ ከግቡ ያልደረሰውን ታላቁን ዓላማ ዕውን ለማድረግ እንደገና ለእንቅስቃሴው ነፍስ ዘርተው፣ የሚያስማማቸው ላይ አብረው ቆመው፣ የማያስሚሟቸውን በሂደት እያጠበቡ ይበልጥ መደራጀትን፣ ዋና ሥራቸው በማድረግ ወደፊት እንዲገሰግሱና በለውጡ ሂደት ላይ

ጋሬጣ ሆነው የቆሙትን ሁሉ በማስወገድ የድሉን ቀን ማቅረብ ነው የሚጠበቅባቸው። እናም ለምን ለሚለው ጥያቄ መልሱ በጉጉት የሚጠበቀው ከዚሁ የለውጥ እንቀሳቃሽና ባለቤት ነውናም ወደዚያው እናመራለን።

ከአርባ ዓመታት በላይ እየፈጀ ያለው የለውጥ እንቅስቃሴ፣ ያነሳቸው አገራዊ ጉዳዮችና፣ ተገቢው መልሳቸው በትግል ይረጋገጥ ዘንድ ያቀረባቸው ጥያቄዎች ዛሬም ቢሆን ገና በቅጡ መልስ ያላገኙ መሆናቸው የሚታይ ነው።

የተፈጥሮ ግዴታ ነውና እያንዳንዱ ሂደት፣ እያንዳንዱ ወቅትና እያንዳንዱ እንቅስቃሴ ሙሉ በሙሉ ራሱን ሆኖ ከሌሎች የሚያያዝበት ፣ የሚለይበት፣ የሚመሳሰልበትና አልፎ አልፎም አንድ የሚሆንበት ዕውነታ መኖሩ አጠያያቂ እንደማይሆን እናስባለን። በጊዜና በቦታ ሁሌም ያልተቋረጠ እንቅስቃሴ እንደመኖሩ፣ የዚያኑ ያህል ደግሞ በሂደት በጣም ተለዋዋጭ ጉዳዮች ሳያቋርጡ እንደሚፈሱ የተፈጥሮ ህግጋት ያስገነዝባሉ።

ላለፉት አርባ ዓመታት በአገራችን እየተካሄደ ያለውን የለውጥ እንቅስቃሴ ገድል ስናስብ፣ እንቅስቃሴው የተጓዘበትን እያንዳንዱን ምዕራፍ በራሱና ለብቻው እንዳለ ማየታችን ተቀዳሚና ዋና ቢሆንም፣ ከሌሎች ምዕራፎች ጋር የሚያያዝበትን ብዙ ገመድ፣ የሚለያይበትን ባህርይና የሚመሳሰልበትን ጎን መርምረን በጎና ጎጂ ገጽታዎቹን በነቂስ ማጤኑ ለቀጣዩ የትግል ምዕራፍ ሂደት አስፈላጊ መሆኑ አይካድም። ይህን ማድረጉ፣ ቀጣዩ የትግል ምዕራፍ ለሂደቱ ካለፈው በጎውን ወስዶ ጎጂውን ደግሞ ዳግም እንዳይከሰትና እንቅስቃሴውን እንዳያጓትት የሚረዱ ዝግጅቶችን ሁሉ የማድረግን አስፈላጊነት የሚያስተምር ይሆናል። ከዚያም በላይ እንቅስቃሴው አላማዬና ግቤ ብሎ ካነገበው ዋና ቁም ነገር ስኬታማ ከመሆኑና ካለመሆኑ ጋር በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በቅጡ የተያያዘ መሆኑንም ጭምር ያጤንበታል።

በእርግጥም በኢትዮጵያ ውስጥ በሂደት በርካታ ለውጦች ተከስተዋል። ሁሉም በየራሳቸው የቆሙና የተለያዩ እንደመሆናችወ በዴሞክራሲያዊው ቀጣይ ትግል ላይ የየራሳቸው የሆኑ ጎጂም በጎም ተጽዕኖዎች አሳድረው አልፈዋል። በዘውድ አገዛዝ ሥር የኖረ ህዝብ በተለይም አገራችንን በመሰለ፣ የዚህን አገዛዝ ባህል አስተሳሰብና ልምድ የበላይነቱን የያዘ በመሆኑ፤ ይህ አመለካከትና አስተሳሰብ በመላው ተራ ዜጋ ውስጥ ብቻ ሳይሆን ለውጥ አምጭውን ሰፊ ህዝብ ጆሮ ኮርኩሮ ባነሳሳው፣ በተወሰነ ደረጃና መጠን ቢሆንም በተማረው የለውጥ ሐዋሪያ ውስጥም የነበረ ነው ለማለት ያስደፍራል። ለዚህም በርካታ ገጠመኞች፣ በለውጡ ወላፈን ሂደት ውስጥ ራሳቸውን በልዩ ልዩ ጊዜ ይፋ እያደረጉ በግለሰብም በድርጅትም መልክ በመሆን ጉልህ የሆኑ ችግሮችንና ጉዳቶችን አድርሰዋል። መሠረታዊና ወሳኝ በሆኑ የትግሉ ዓላማዎችና የትግሉ አቅጣጫዎች ላይ የነበሩ ልዩነቶች እንዳሉ ሆነው፣ ከዚያ በመለስ የነበሩ ጉዳዮችን፣ በአግባቡ ለመያዝና ለማስተናገድ እንዳይቻል፣ ያደረጉ የግለሰቦች ኋላ ቀር ባህርያት ማለትም፣ ሁሉን አውቃለሁ ማለት፣ የራስን አመለካከት/አስተሳሰብ ብቻ የበላይ ለማድረግ መጣር፣ ለሕግና ለደንብ አለመገዛት፣ ራስን ከህዝብ ጥቅምና ፍላጎት ማስቀደም፣ በህዝብ ተገልጋይ እንጂ ለህዝብ አገልጋይ

አለመሆን፣ ጎጂ አመለካከታቸውና አስተሳሰባቸው ተቀባይነት ሲያጣ በግድ ለመጫን አጥፊ እንቅስቃሴዎች ላይ መሰማራት፣ ...ወዘተ በገሃድ የታዩ የቅርብ ጊዜ ትዝታዎች ናቸው። ዛሬም ድረስ በትግሉ ውስጥ ዘልቀው በየምዕራፉ ትግሉን እየጎተቱ እንዳሉ አሉ። እነዚህ ባህርያት ከዲሞክራሲያዊነት አስተሳሰብ ጋር ጨርሶ የተጣሉ በመሆናቸው፣ የለውጡን እንቅስቃሴ በመቀልበሱ ላይ ወሳኝ ባይሆኑም በአጋዥነት ያገለገሉ ናቸው ብሎ ማለት ከእውነት የራቀ አይሆንም። ዛሬም በእንቅስቃሴያችን ውስጥ መኖራቸውን ከተቀበልንና የሚያስከትሉትም ጉዳት ላይ ከተስማማን፣ ከእንግዲህ ትግሉን እንዳይጎዱ በአግባቡ ልንታገላቸውና ከጨዋታው ውጭ ልናደርጋቸው ይገባል።

ከላይ ለጠቀስነው ጉድለት ወይም ድክመት እንደምሳሌ መጥቀስ ቢያስፈልግ፣ በዚያን ወቅት የትግሉ ተዋንያን በነበሩ ድርጅቶች ውስጥ፣ በመስራችነት፣ በአመራርና በአባልነት ጭምር የተንቀሳቀሱ ግለሰቦች፣ የነዚህ ባህሪያት ተሸካሚ ሆነው ከባድ ጉዳት አድረሰው አልፈዋል። አንጃንነት፣ አድርባይነት፣ ባንዳነት፣ በታኝነት ወዘተ... የመሳሰሉት ተሰማርተው በትግሉ ላይ ጉዳት ማደረሳቸው የታወቀ ነው። ዛሬም ቢሆን ወሳኝና መሰረታዊ በሆኑ ጉዳዮች ላይ ወገቤን በማለት ለወያኔ እንጎንበስ ብለው ልዩነትን ያቀነቀኑ ጥቂት አባላትና በአመራር ደረጃ የነበሩ ግለሰቦች፣ ህግና ደንብን ጥሰው በድርጅት ውስጥ ድርጅት ፈጥረው በአንጃኝነት በመንቀሳቀስ ትግሉን ጎድተዋል።

ሌላው በቅጡ መጠቀስ የሚገባው ጉዳይ ቢኖር፣ ይህ የሥር-ነቀል የለውጥ እንቅስቃሴ ያፈራቸው እጹብ ድንቅ ተራማጅ ምሁራን የነበሩና ዛሬም ያሉ መሆናቸው እንዳለ ሆኖ፣ ለትግሉ ያበረከቱትንና እያበረከቱ ያሉትን ብሎም የከፈሉትን መስዋዕትነት እየዘከርን ፣ በሌላ በኩል በምሁርነት ስም ከላይ ጎጂ ያልናቸውን ባህርያት የተላበሱ ቁጥራቸው ቀላል ያልሆነ ምሁር ነን ባዮች በእንቅስቃሴው ውስጥ ተሰግስገው የማደናገሩንና የማጓተቱን ሥራ እስከዛሬም በስፋት ተያይዘውታል። እነዚህንም በአግባቡ እንቅስቃሴው ሊታገላቸው ይገባል።

ኢሕሕፓ ለዴሞክራሲ የሚታገል ድርጅት ነው። በመሆኑም፣ የእያንዳንዱ ዜጋ (የግለሰብ) ነጻነት፣ ማለትም የመናገር የመጻፍ የመደራጀት፣ የመማር፣ የመንቀሳቀስ እንዲያው በጥቅሉ ያለገደብ መብቱ እንዲከበር ይታገላል። ይህ እንዲሟላለትም የሚያስችለው ገቢ እንዲኖረውም አስተማማኝ ሥራ ሊኖረው ይገባልም ይላል። ቢታመም የሚታከምበት፣ ቢያጣ የሚደጎምበት ሁኔታ ሁሉ ሊመቻችለት እንደሚገባም ያሰምርበታል። ይህ ሁሉ ግን ከፍትሃዊነት ጋር የተቆላለፈ እንደሆነም ይገነዘባል። ያም በመሆኑ ማንም ዜጋ ባፈተተውና በሚመስለው መንገድ ሁሉ የመደራጀት መብቱ ላይ ኢሕአፓ ጥያቄ የሚያነሳ አይሆንም። ያ ማለት ግን ባካሄዳቸውም ሆነ በድርጊታቸው እንቅስቃሴውን እየጎተቱ ወይም በተጨባጭ እየጎዱ ሲገኙ እጁን አጣጥፎ ይቀመጣል ማለትም አይደለም። ስለሆነም ዛሬ በውጭም በውስጥም እራሳቸውን በልዩ ልዩ መልክ ያደራጁና ባሻቸው መንገድ እየተንቀሳቀሱ ያሉ ድርጅቶች፣ እንቅስቃሴያቸው የጋራ የሆነችውን ኢትዮጵያ እስከተመለከተ ድረስ፤ አቅጣጫቸውና ድርጊታቸው

በተግባር፣ በተጨባጭ ለዴሞክራሲና ለአገር አድን የሚደረገውን ትግል እያጎለበተ ወይም እየረዳ መሆኑን እንዲያዩ እስካሁን የተጓዙበትን መንገድ እንዲገመግሙ ወቅቱ ግድ ይላቸዋል።

የአምባገነንነት አዙሪት ሳያቋርጥ እየተፈራረቀ ባደረሰው ከፍተኛ እመቃና በደል የተነሳ ለለውጥ የሚታገሉ ኃይሎች አዕምሮቸውን እንዳያሰሉ፣ አመለካከታቸውን እንዳያሰፉና እንዳያሳድጉ፣ በጤናማ የሃሳብ ፍጭትም የዕውቀት አድማሳቸው እመርታ እንዳያገኝ በመደረጉ፣ ይህ ሁኔታ የፖለቲካ ልምድና ብስለት እንዲቀጭጭ ያደረገበት ከመሆኑ ባሻገር፣ ትግሉን ወደ ኋላ በመጎተቱ ላይ ቀላል የማይባል አስተዋጽኦ አድርጓል። በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ፣ አስከፊውን የአምባገነን አገዛዝ ዕድሜ ለማራዘምም ረድቷል። ዛሬ በውስጥም በውጭም በሰፊው ተበራክቶ ያለው ቅጥ አምባሩ የጠፋ መራኮት፣ ከአርባ አመት የለውጥ ትግል በኋላም እንዲህ ገዝፎ ስናይ የሚያሳዝነን ቢሆንም የትግላችን አንዱ ድክመት ወይም ችግር መሆኑን እንረዳለን። በመለስተኛ ደረጃ ሊቀመጥ የሚችል ችግር ነው ብለን ስለምናስብ፣ ትግሉ በአግባቡ ለመወጣት ጎጂነቱንም በማስወገድ እንቅስቃሴው በሁሉም መስክ እንዲጎለብትና እንዲጠናከር ሁሉም የበኩሉን አስተዋጾኦ ማድረግ ግን ይጠበቅበታል እንላለን።

አምባገነንነትና ዴሞክራሲ አጥፊና ጠፊ ናቸው። የአንዱ ህልውና ለሌላው ሞት ነው። ለምዝብሩ የኢትዮጵያ ህዝብ አምባገነንነት አብሮት ለዘመናት የኖረ፤ ሸብቦት፣ እግር ከወርች አስሮት፣ እንደልቡ ያሻውን እንዳይሆን ቀፍዶት፣ አንተ አታውቅም ብሎት፣ አልፋና ኦሜጋው እኔ ያልኩት ብቻ እንጂ ነው፣ ውልፍች ብትል መቀመቅ ፣ አይ ካልክ ዘብጥያ፣ ...ሌላም ሌላም ሆኖ ጭራሽ ደብዛውን እያጠፋው የኖረ የምድር ላይ ሲኦል ሆኖበት እንዳለ ያለ መሆኑን የሚነግረው አይሻም። ከአጼው በፊት በአጼው ጊዜ፣ ከዚያም በኋላ በተከታታይ በጫንቃው ላይ የተጫኑትን ሥርዓቶች/አገዛዞች አጥብቆ ይጠላል፤ ሁሌም በምሬት ታግሏቸዋል። ዛሬም ይጠላቸዋል - አምባገነንነት የሚወደድ፣ የሚፈቀር ባለመሆኑ! ዛሬም ለአንዴም ለሁሌም ከጫንቃው ላይ ለማስወገድ አጥብቆ እየታገላቸው ይገኛል።

የህዝብ የሥልጣን ምንጭነት፣ የህዝብ የሥልጣን ባለቤትነት፤ የኢትዮጵያ ሉዓላዊነትና ድህንነት፣ የህዝቧ በዕኩልነትና በአንድነት መኖር፣ ብሎም ዴሞክራሲያዊት ሆና ሰላምና ፍቅር ሰፍኖባት በሁሉም መስክ በአድገት የገሰገሰች የታፈረች የተከበረች ታላቅ አገር እንድትሆንና ለመጪው ትውልድ በአለኝታነትና በኩራት እንድትተላለፍ ኢሕአፓ አጥብቆ ይፈልጋል። ለኢሕአፓም የትግሉ አልፋና ኦሜጋ ይኼው ነው !

ኢሕአፓና ሰፊው ምዝብር የኢትዮጵያ ሕዝብ ለዚህ ታላቅ ቁም ነገር መሳካት ሲሉ እጅግ በርካታ መስዋዕትነትን ከፍለዋል። የአምባገነንነትን አባዜ ከዚያች ምድር ለማጥፋት ጽናትና ቀጣይ መስዋዕትነት መጠየቁ ዛሬም ቢሆን ያለ ነው። ዛሬ የአፍላ ጊዜያቸውን ለዚህ ታላቅ ቁም ነገር ለማዋል ብዙ የደከሙ የፋሽስታዊው ጽልመት አዳከሚቸው ፣ ዘረኝነትና አምባገነንነት አንዳሻው ሲናጥጥ ከዳር ሆነው ትግሉን እርግፍ አርገው ትተው ስናይ የሚያሳዝነን ቢሆንም፣ ላለመታገል ያላቸውን መብት ግን በጥያቄ ውስጥ የምናስገባው አይሆንም። ሌሎች ጭራሽ ከዘረኛውና አምባገነኑ ቡድን ጋር፣ ሆዳቸውን ብለው ተቃቅፈውና አጎንብሰው የትግሉ ነው ህይወቴ ያላሉትን ያህል ትግሉን ሲገድሉ ስናስተውል ግን ልባችን

ይደማል። ያም ሆኖ፣ ዛሬም ቢሆን የገቡትን ቃል ኪዳን ለአፍታም ሳያጥፉ ፣ ለዚህ ከትልቅም ትልቅ ለሆነ ቁም ነገር፣ ለፍትህ ፣ ለነጻነትና ለእኩልነት የሚደረግን ትግል የኔ ብለው ክቡር ህይወታቸውን የሰዉትን ሁሉ እየዘከሩ፣ በጽናት ትግሉን ያስቀጠሉና የቀጠሉትን፣ ቀሪውን የትግል ዘመን ከዳር የሚያደርሱ ተረካቢ ጎልማሶች ለጋ ህይወታቸውንና ትኩስ ጉልበታቸውን ለዴሞክራሲና ለአገር አድን ትግሉ ለማዋል የተዘጋጁ ከተፎዎች መኖራቸውን ስናጤን፤ ትግሉ የመረረውን ያህል ይምረር እንጂ፣ ያ በ66ቱ የናኘው የነጻነት አየር፣ የብሩህ ተስፋ ጸዳል በአምባገነንነት መቃብር ላይ እንደሚያብብ ከቶ የሚያጠራጥረን አይሆንም።

እንደሚታወቀው ለአምባገነንነት አገዛዝ እንግዳ ባንሆንምና፣ ሁሉም ዓይነት አምባገነንነት አንድ የሚያደርጋቸው የጋራ ባህሪይ እንደመኖሩ ፣ አንዱ ከአንዱ የሚለይበት ሁኔታ እንዳለም እንደ አዲስ የሚነገር አይደለም። ለዚህ እየኖርንበትና እየታገልነው ያለንበትን ሁኔታ እንደገና ዋቢ አድረገን እንድናቀርብ ከቶም ቢሆን የሚጠበቅ አይመስለንም። እናም የወቅቱ አምባገነን ካለፉት አምባገነኖች የሚለይበት እንደመቋሚያው አድርጎ የተንተራሰበት የዘር ፖለቲካ፣ ለዴሞክራሲ በሚደረገው ትግል ላይ ብቻ ሳይሆን የአገር ህልውናንም ጭምር የሚፈታተን ሆኖ በመገኘቱም ነው። ዛሬ ኢትዮጵያ የደረሰችበትን አደገኛ ሁኔታ በቅጡ ተገንዝበው፣ በአርማሞ አመለካከትና በምን ይመጣል አባዜ ሳይዋጡ፣ የፋሽስቱ ወታደራዊ መንግሥት ርዝራዦች አባወራዊነትን፣ የአንድ ሰሞን የወያኔ አገዛዝ መሥራችና ለክፉ ተግባሩ ሁሉ መሃንዲስ ሆነው ሲባጁ የቆዩትን፣ አንዳችም ጊዜ ለዚህ ጥፋታቸው የኢትዮጵያን ህዝብ በቅጡ ይቅርታ የመጠየቅ ሃሳቡ እንኳን የሌላቸውን አጥፊዎች፣ በስመ ተቃዋሚ የወያኔን ሎሌነት ለመተካት የውጭ ኃይላትን ድጋፍና ቡራኬ እያገኙ ያሉትንና ወደፊትም ይህንኑ ለመቋደስ የሚቋምጡትን ሁሉ የማጀቡና የማዳነቁን ዘመን፣ መርሳትን አየረሱ በተደጋጋሚ ስህተትን የመፈጸም አባዜን፣ መግታት ካልቻልን ሁሌም ነገሩ ሁሉ ውሀ ቢወቅጡት እምቦጭ እየሆነብን ትግሉ በመጓተትና በመዳከም አዙሪት ውስጥ እንዲዳከርና ለአምባገነን አገዛዝ ተመቻችቶለት በሁኔታው ይበልጥ እንዲፈነጭ፣ ብሎም እንዳሻው መፍለጥ መቁረጡን እንዲቀጥልበት አድሉን አናሰፋለታልን። ያ እንዳይሆን ሁሉም ለአገሩ የሚቆረቆርና አገሩን ከልቡ የሚወድ ዜጋ፣ የወደፊት ብሩህ ተስፋዋን የሚመኝ፣ ለደህንነቷ ሲባል የሚደርሰውን ሁሉ ለመክፈል የተዘጋጀ ራሱን እንደገና መርምሮ ድክመቱን ተረድቶ፣ በተግባርም ዳግም ላይደግመው ትምህርት ወስዶ፣ የራሱን አንጻ ግራንጻ ሁሉ በጓዳው አስቅምጦ፣ ለቀረበለት የአገር አድን ጥሪ "አለና !" ብሎ ቀበቶውን ጠበቅ አድርጎ መገኘት የመልካም ዜግነት ግዴታ ነው።

የኢትዮጵያ ህዝብ እንድማናቸውም ሌሎች ህዝቦች ሁሉ የሚፈልገውንና የሚበጀውን፣ የሚጎዳውንና የማያዋጣውንም ጭምር አሳምሮ ያውቃል። ቀናኢ ፣ አስተዋይ፣ ታጋሽ ፣ ቆራጥ፣ ራሱንና ክብሩን ሁሌም ከፍ አድርጎ የሚጠብቅ ኩሩ ህዝብ እንደሆነ ምስክርነት የሚያሻው አይደለም። ህዝባችን ደጋግመን እንደምንጠቅሰውና እንደታሚታወቀው፣ የሰብዓዊ መብቶቹ ያለምንም ገደብ እንዲከበሩለት ይሻል። የመሥራት፣ እንደልቡ ከቦታ ቦታ የመንቀሳቀስ፣ ያሻውን የማመን፣ ጤንነቱን የመንከባከብ ነጻነቱ

ባጠቃላይ በነጻ ዜግነቱ ላይ ምንም ልጓም እንድይበጅለት የፍትኅና የሕገመንግሥት ሁኔታዎች እንዲመቻቹለትም የግድ ይላል። የማወቅና የመማር መብቱ ተከብሮ፣ በሥነ ጽሁፍ፣ በእደጥበብና በልዩ ልዩ ዘርፎች ወደፊት እንዲገሰግስ፤ ለጥበብ፣ ለምርምር፣ ለኪነት ምቹ ሁኔታ ይፈልጋል። በጥቅሉ ዛሬ ህዝባችን ዴሞክራሲን በአምባገነኑ በዘረኛው የወያኔ አገዛዝ መቃብር ላይ ለመትከል አጥብቆ ይሻል።

ይህ ዛሬ ቁልጭ ብሎ ያለውና ዋነኛው ማለትም በወያኔ አገዛዝና በሰፊው ህዝብ መካከል ያለው የማይታረቀው ቅራኔ፣ መፍቻው፣ በሰፊው በተደራጀና በተባበረ፣ ወዳጅና ጠላቱን በቅጡ በለየ፣ ህዝባዊ ትግል ብቻ ነው። በመሆኑም ኢሕአፓ ለኢትዮጵያ ህዝብ ባጠቃላይ እንዲሁም ኢትዮጵያን ለሚሉ ሀገር ወዳዶች ሁሉ፣ ትግሉን በስፋት ተቀላቅለው የሚከፈለውን ሁሉ በመክፈል ኢትዮጵያን እንዲታደጉ አበክሮ ያሳስባል። ለስሙ ሳይሆን በእርግጠኛነት የኢትዮጵያን ህዝብ ጥቅምና ፍላጎት ለማስቀደም ተደራጅተናል ለሚሉ ሁሉ፣ ትግሉ በሁሉም አቅጣጫ እንዲጎለብትና እንዲጠናከር የማስተባበርና አቅጣጫ የማሳየት ብቃታቸውን እንዲለግሱት አጥብቆ ይጠይቃል፡፡ ኢሕአፓ ይህን ከፍተኛ የዜግነት ግዴታ በሚመለከት በልሳኑ ዴሞክራሲያ ቅጽ 16፣ ቁጥር 2 ግንቦት 1982 እትሙ እንዲህ ብሎ አስቀምጦት ነበር።

"በጥንታዊ ሥልጣኔዋ፣ በነፃነት ዓምድነቷ አሻቅበው የሚያዩዋት፣ የሚኮሩባት፣ ተገን ፀወን የምትሆን ሃገር መሆኗ ቀርቶ የመጨረሻይቱ ኋላ ቀር፣ ነዳይ ምስኪንና ምፅዋተኛ፣ የሁከት መናኸሪያ፣ የእድገት መቀበሪያ ሁና፣ ቁልቁል በአድንኖ፣ ዓይንን ሰብሮ ስለሚመለከቷት፣ ትቢያ ላይ ስለወደቀች አገር፣ ቁጭት ለሚሰማው ኢትዮጵያዊ ሁሉ የጓዳውን ጣጣ ፈንጣጣ፣ የግሉን አንጃ ግራንጃ ወደ ዳር ትቶ፣ ትቢያዋን አራግፎ፣ ርስሕቷን ከልቶ፣ በትር ምርኩዝ ሁኖ በእግሯ ተደላድላ እንድትቆም አድርጎ ሃገር አለሻ ለማለት መብቃት፣ የቀረበለት ቁልጭ ያለ የሞት የሽረት ጥያቄ ነው። ከዚሁ አገርን እንደ አገር ከማቆም ጥያቄ ጋር አብሮ መመለስ ያለበት፣ ይህችው ሃገር ቆማስ ወዴት ነው በምንድን ነው የምትራመደውስ የሚለውንም ጭምር ነው። ኢትዮጵያ ጤና እንድትገዛ፤ ሕዋሳቷ ሕይወት አግኝተው እንዲነዝሩ፣ እጆቿን ወደ ጥበብ አድማስ እንድትዘረጋ፣ ያለመሰናከል በእድገት ጎዳና እንድትራመድ ኋላ የቀረችውን ያህል እንድትገሰግስ፣ አመንምኖ ከዚህ ድቀት የጣላትን የጦርነትንና የሁከትን መዳረሻ ማጥፋት ዳግመኛም የማይመለስበትን መላ መምከር የግድ ነው።"

ይህንና ይህንን ማድረግ ሲቻል ብቻ ነው አልወገድ ያለው አምባገነንነት ለአንዴም ለሁልጊዜም ከሥሩ ተመንግሎ ሊነቀል የሚችለውና አልከሰት ያለው ዴሞክራሲ በኢትዮጵያ ዕውን ሆኖ በሂደት ለምልሞና አብቦ ፍሬ የሚያፈራው፤ ፍሬውም የሚበላው።

አምባገነንነት በተባበረ ትግላችን ይወገዳል!
ዴሞክራሲም ያለጥርጥር በኢትዮጵያ ይከሰታል!
ድል ለሰፊው ህዝብ ትግል!!